IBO IB DIPLOMA PROGRAMME
PROGRAMME DU DIPLÔME DU BI
PROGRAMA DEL DIPLOMA DEL BI

M03/166/H(2)

**AMHARIC A1 – HIGHER LEVEL – PAPER 2**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU SUPÉRIEUR – ÉPREUVE 2**
**AMHARE A1 – NIVEL SUPERIOR – PRUEBA 2**

Friday 23 May 2003 (afternoon)
Vendredi 23 mai 2003 (après-midi)
Viernes 23 de mayo de 2003 (tarde)

2 hours / 2 heures / 2 horas

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a commentary on one passage only.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- Ne pas ouvrir cette épreuve avant d'y être autorisé.
- Rédiger un commentaire sur un seul des passages.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario sobre un solo fragmento.

ከሚከተሉት በአንዱ ላይ ሀተታ ጻፍ(ጻፊ)፡፡ መልስህ(ሽ) በክፍል 3 ባጠናሃቸው(ሻቸው) ቢያንስ ሁለት ሥራዎች ላይ መመሥረት አለበት፡፡ በክፍል ሁለት ሥር ካለ አንድ ተመሳሳይ ሥነጽሑፍ ዘር መጠነኛ ማጣቀሻ ማስገባት ይፈቀዳል፤ ይህ ግን በክፍል 3 ሥር ከሚገኙት ቢያንስ ሁለት ስራዎች በተጨማሪነት ብቻ መሆን አለበት፡፡ ሌሎች ሥራዎችን ማጣቀስም ይቻላል፡፡ ሆኖም የመልስህ(ሽ) አቢይ ክፍል ሌሎቹ ሥራዎች ላይ መመስረት የለበትም፡፡

ድራማ

1. ተከታዩን

(ሀ) ትራጀዲ በተመልካቹ ላይ የሀዘን ስሜት የሚፈጥር ሲሆን ኮመዲ ደግሞ ሳቅን ይፈጥራል፡፡ ሆኖም ትራጀዲም ሆነ ኮመዲ የህይወትን የተለያየ ገጽታ የሚያሳዩ በመሆናቸው አይበላለጡም፡፡ ይህንን ሀሳብ ያነበብካቸውን ተውኔቶች ምሳሌ በማድረግ አስረዳ፡፡

ወይም ቀጣዩን ምረጥ፡፡

(ለ) ገፀባህሪ፥ ምልልስና ትልም የድራማ ዋነኛ አላባውያን ናቸው፡፡ ሦስቱ በጋራ የተውኔቱን አለም ይፈጥራሉ፡፡ ያነበብካቸውን ሁለት ድራማዎች በመውሰድ እነዚህ አላባውያን ያላቸውን ሚና በማነጻጸር ግለጽ፡፡

ረጅም ልቦለድ

2. ተከታዩን

(ሀ) የልቦለድ ገፀባህሪ ፍጹም ሊሆን አይገባውም፡፡ እንደማንኛውም የገሀዱ አለም ሰው ጠንካራና ደካማ ጎን ሊኖረው ይገባል፡፡ የዚህን ሀሳብ ትክክለኛነት ያጠናሀቸውን ሁለት ልቦለዶች በማነጻጸር አሳይ፡፡

ወይም ቀጣዩን ምረጥ፡፡

(ለ) የልቦለድ ግጭት የታሪኩ የጀርባ አጥንት ነው ይባላል፡፡ ያነበብካቸውን ሁለት ልቦለዶች በመጥቀስ በዚህ ሀሳብ ምን ያህል እንደምትስማማ አስረዳ፡፡

ሥነግጥም

3. ተከታዩን

(ሀ) ግጥም እጅግ ቁጥብና እምቅ ነው ይባላል፡፡ እነዚህን የግጥም ባህሪያት ካነበብካቸው ግጥሞች ጋር በማያያዝ ግለጽ፡፡

ወይም ቀጣዩን ምረጥ፡፡

(ለ) ግጥሞች ሙዚቃዊና ስሜትን ገላጭ ናቸው፡፡ ያጠናሀቸውን ሦስት ግጥሞች ይህንን ሀሳብ መሠረት በማድረግ አነጻጽር፡፡ ከላይ የተገለጸው ሐሳብ ምን ያህል እውነት መሆኑን ግጥሞቹን በምታነፃፅርበት ጊዜ ተመልከት፡፡

ስድንባብ (ከረጅምና አጭር ልቦለዶች ሌላ)

4. ተከታዩን

(ሀ) የፀሐፊው የቃላት ምርጫና የአጻጻፍ ስልት በአንባቢው ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ይኖራል። ባነበብካቸው ስራዎች ውስጥ የደራሲው የቃላት ምርጫ፥ ሐሳብን የመግለጽ ችሎታና የአጻጻፍ ስልት ምን ያህል ተጽእኖ አሳድሮብሀል?

ወይም ቀጣዩን ምረጥ፡

(ለ) ፀሐፊዎች በስራዎቻቸው የሚገልጹት የተመለከቱትን ብቻ በመሆኑ አንድን ጉዳይ የሚገልጹት ከራሳቸው አኳያ ነው። በዚህ ሀሳብ ምን ያህል ትስማማለህ?

አጭር ልቦለድ

5. ተከታዩን

(ሀ) በረጅም ልቦለድ ረጅም ታሪክ የሚቀርብ ሲሆን በአጭር ልቦለድ በዋናነት የሚቀርበው አንድ የተወሰነ ሁኔታ ወይም ስሜት ነው። የተወሰነ ሁኔታ ወይም የተወሰነ ስሜት በመምረጥ አጭር ልቦለዶቻቸውን ያቀረቡ ደራሲዎች ስራዎች ላይ አስተያየትህን ስጥ።

ወይም ቀጣዩን ምረጥ።

(ለ) በአጭር ልቦለድ ገፀባህርያትን በጥልቀት ለመሳልና የህይወታቸውን የተለያየ ገጽታ ለማሳየት አይቻልም። በመሆኑም የአጭር ልቦለድ ደራሲ ትኩረቱ በተለምዶ በሚታወቁ ገፀባህርያት ላይ ይሆናል። እስካሁን ካነበብካቸው አጭር ልቦለዶች በመነሳት በዚህ ሀሳብ ምን ያህል ትስማማለህ? ያነበብካቸው አጭር ልቦለዶች ገፀባህሪያቶቻቸውን እንደምን ስለዋቸዋል?

ሁለገብ (አጠቃላይ)

6. ከሚከተሉት አንዱን መርጠህ(ሽ) መልስ(ሽ)

(ሀ) የፈጠራ ስራ የገሀዱ አለም ነፀብራቅ ነው ይባላል። በሌላ በኩል ደግሞ የፈጠራ ስራ በደራሲው ምናብ የታለመ እንጂ በእውን የተከሰተ አይደለም የሚል አስተያየት ይሰጣል። እነዚህ ሁለት ሐሳቦች ይደጋገፋሉ ወይስ ይቃረናሉ? ለምን? ሀሳብህን በምሳሌ አስረዳ።

ወይም

(ለ) ሰዎች ሁሉ አንድን የስነጽሑፍ ስራ በእኩል ደረጃና በተመሳሳይ ሁኔታ የማይረዱት ለምን ይመስልሀል?

ወይም

(ሐ) ደራሲዎች ጊዜን እንዴት እንደሚጠቀሙና በሚተረከው ታሪክ ጣልቃ ያለፈ ታሪክ በማምጣት ስራቸውን እንዴት የተዋጣ ለማድረግ እንደሚጥሩ በክፍል ሦስት ያነበብካቸውን ሥራዎች በምሳሌነት በመጥቀስ አሳይ።

ወይም

(መ) የምታነበውን የስነጽሑፍ ስራ ደራሲ ፆታ ማወቁ ምን ያህል ጠቃሚ ይመስልሀል? የፆታ አድልዎን ወይም ገለልተኛነትን የሚመለከቱ ምሳሌዎችን ካነበብካቸው ስራዎች ውስጥ ስጥ።